Amharic

# 2022–2023

የተማሪ መመሪያ

# የጾታ ማንነት

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

www.montgomeryschoolsmd.org

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

VISION ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ መማርን እናበረታታለን።

ተልእኮ

እያንዳንዱ ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ ይኖሯታል።

ዋና ዓላማ

ሁሉንም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው እንዲዳብር/ እንዲበለጽግ ማዘጋጀት፡ ፡

ዋነኛ እሴቶች

መማር/እውቀት
ግንኙነቶች
አክብሮት
ልቀት
ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት

Board of Education የትምህርት ቦርድ

Ms. Brenda Wolff ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ
President ፕሬዚደንት

Ms. Karla Silvestre ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ
Vice President ም/ፕሬዚደንት

Dr. Judith R. Docca ዶ/ር ጁዲት አረ. ዶካ

Mrs. Shebra L. Evans ወ/ሮ ሸብራ ኤል. ኢቫንስ

Ms. Lynne Harris ሚ/ስ ለይኔ ሃሪስ

Dr. Scott Joftus ዶ/ር ስኮት ጆፍተስ

Mrs. Rebecca K. Smondrowski ወ/ሮ ርብቃ ኬ. ስሞንድሮውስኪ

Mr. Arvin Kim ሚ/ር አርቪን ኪም
Student Member ተማሪ አባል

Montgomery County Public Schools (MCPS) Administration
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አስተዳደር

Monifa B. McKnight, Ed.D. ሞኒፋ ቢ. መክነይት ዶ/ር
Superintendent of Schools የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

Mr. M. Brian Hull ሚ/ር ኤም. ብረያብ ሁል
Chief Operating Officer ዋና የሥራ ኃላፊ

Patrick K. Murphy, Ed.D. ፓትሪክ ኬ. መርፊ ዶ/ር
Deputy Superintendent ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

Mr. Brian S. Stockton ሚ/ር ብረያን ኤስ. ስቶክተን
Chief of Staff ዋና የሠራተኞች አስተዳደር ኃላፊ

Mrs. Stephanie P. Williams ወ/ሮ ስቴፈኒ ፒ. ዊልያምስ
General Counsel ጀነራል ካውንስል

Ms. Elba M. Garcia ሚ/ስ ኤልባ ኤም. ጋርሽያ
Senior Community Advisor ዋና የማህበረሰብ ጉዳይ አማካሪ

Dr. Patricia E. Kapunan ዶ/ር ፓትሪሽያ ኢ. ካፑናን
School System Medical Officer የትምህርት ቤቶች ጤና ጥበቃ ኃላፊ

850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# 2022–2023

## የተማሪ መመሪያ

# የጾታ ማንነት

**በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

www.montgomeryschoolsmd.org

የ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ ጾታ ማንነት መመሪያበ MCPS ድረ-ገጽ ላይ በ እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ቻይንኛ፣ ኮሪያንኛ፣ ቬትናምኛ፣ በአማርኛ፣ እና በፖርቱጋልኛ ይገኛልwww.montgomeryschoolsmd.org/students/rights/

የተማሪ ጾታ ማንነት መመሪያዎች (አማርኛ)

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

© ሰፕቴምበር 2022
Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland

ሰፕቴምበር 2022

ውድ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች

በ 2021–2022 የትምህርት ዓመት በሳምንት አምስት ቀናት በአካል ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ጠቃሚ ነበር፣ ነገር ግን ያለ ተግዳሮቶች አልነበረም። እንደ ማህበረሰብ፣ የሁላችንንም ደህንነታችንን ለመጠበቅ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጭ በሚከናወኑ ስራዎች፣ ባለው የወረርሽኝ አስገዳጅነት መመሪያዎችን በመቀየር አስተካክለናል። እንደ ማህበረሰብ ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት እንዲቻል በሁሉም ስራ ዘርፍ መተባበር እና በአጋርነት ጥረት ማድረግ ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ ሆኗል።

የሞንጎመሪ ካውንቲን ማህበረሰባችንን ደማቅ ልዩነት መቀበል መቀጠል አለብን እና ሁሉም ተማሪዎች ተቀባይነት፣ ደህንነት እና ክብር የሚሰማቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። ይሄ ዋና መሰረታዊ መሆን ያለበት እያንዳንዱ ተማሪ ለስኬት እና ለመበልፀግ ትርጉም ያላቸው እድሎች ላይ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲያገኝ ነው።

ይህ ቁርጠኝነት በሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣  ስለ ፀረ-መድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት እና ባህላዊ ብቃት ኮድ የተሰየመለት ነው፣ እናም  ፍትሃዊነት፣ አቃፊነት እና ለሁሉም ተቀባይነት ለመፍጠር፣ ለማዳበር የማህበረሰባችን የረጅም ጊዜ ጥረቶች እንደገና ይረጋግጣል። የዚህ ቁርጠኝነት አካል የሆነውም የእኛ የ LGBTQ ተማሪዎች ያለ አድልዎ፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም መንቋሸሽ የጾታ ማንነታቸውን መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው። የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እንደመሆናችን መጠን፥ የሥርዓተ -ፆታ ማንነት ጉዳዮችን በመገንዘብ እና በማክበር ቁርጠኛ ነን፤ የሥርዓተ -ፆታ ማንነትን በተመለከተ ከተማሪዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ሁሉንም ምክንያታዊ ማመቻቸቶችን ማድረግ፤ እና ለሁሉም ተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ቅንነት የተሞላበት እና በመከባበር የመማሪያ አካባቢዎችን ለመፍጠር ስንጥር የተማሪን ግላዊነት እና ምስጢራዊነት በመጠበቅ ነው።

ከመልካም ወዳጅነት ጋር

Monifa B. McKnight

……………..

# ጉዳዩ፡-

ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . i
መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ትርጓሜዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ጾታ ከቀየሩ እና ፆታቸውን ይፋ ከማያደርጉ ተማሪዎች ጋር በንቃት መሥራት . . . . . . . . . . . . . . 2
የሥርዓተ -ፆታ ድጋፍ ዕቅድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
ከቤተሰብ ጋር መግባባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
ግላዊነት እና መረጃ ይፋ ማድረግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
ስሞች/ተውላጠ ስሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የሰራተኞች ግንኙነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
ቋሚ የት/ቤት ሪከርዶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የአለባበስ ኮድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
በጾታ ላይ የተመሠረቱ እንቅስቃሴዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
ለጾታ የተለዩ ቦታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
አዲስ ግንባታ/እድሳት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት ክፍሎች እና የቡድን ስፖርቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
ክለቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
ከቤት ውጭ ትምህርት/የሌሊት የመስክ ጉዞዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ዛቻ እና የማስፈራራት ምርመራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
ሠላማዊ ቦታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
የሰራተኞች ድጋፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

# ፈጣን የማገናዘቢያ መመሪያ

## የተማሪዎች መገልገያዎች

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ ለድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመሮች
24 ሰዓት መረጃ፣ ወደሚመለከታቸው ማስተላለፍ እና ድጋፍ ሰጪ ውይይት

Maryland Crisis Hotline/EveryMind/ . . 301-738-2255 and https://www.every-mind.org/
በድረ-ገጽ ላይ ሰራተኛ የሚያነጋግሩበት የስልክ መስመር እና 24 ሰዓት የውይይት አገልግሎት ክፍት መስመር።

Montgomery County Crisis Center - የሞንትጎመሪ ካውንቲ የድንገተኛ ሁኔታ ማእከል 240-777-4000
የድንገተኛ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች ድንገተኛ የስልክ ጥሪ መስመር:-
Youth Crisis Hotline of Montgomery County
301-738-9697
24 ሰዓት በስልክ ነቅቶ የማዳመጥ እና ሪፈራል አገልግሎት በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት የምስጢር አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል።

### የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ:-

MCPS ሲስተም አቀፍ የአደጋ ጊዜ ማኔጅመንት ዲፓርትመንት
240-740-3066
የ MCPS ትምህርት ቤቶችን እና ድ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የ MCPS ቢሮ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የተማሪ ደህንነት እና ህግ ማክበር:- SWC@mcpsmd.org or TitleIX@mcpsmd.org . .240-740-3215
የ MCPS ዲስትሪክት አቀፍ የ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ግንኙነት ኃላፊ። የተማሪ ደህንነት እና ስርአት ማክበር ድረ-ገጽ https://www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/. SWC ከትምህርት ቤቶች፣ ከጀነራል ካውንስል ጽ/ቤት እና ከሌሎች የ MCPS ጽ/ቤቶች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር እንደ ፖሊሲዎች ፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች፣ ከሰዎች ግንኙነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ከመተግበር አኳያ፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (Title IX ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ እና ማስፈራራት፣ የሕፃናትን በደል እና ቸልተኝነትን መገንዘብ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻና-አድሏዊነት፣ የጥላቻ እና የተማሪ የጾታ ማንነት ጉዳዮችን በሚመለከት ከላይ ከተጠቀሱት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox:- CyberSafety@mcpsmd.org
በ MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔትዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline 1-800-843-5678
ለወሲባዊ ድርጊቶች፣ ከቤተሰብ ውጭ ያለ ልጅ ወሲባዊ ጥቃት፣ የልጆች ወሲባዊ ሥዕሎች፣ የልጆች ወሲባዊ ቱሪዝም፣ የሕፃናት ወሲባዊ ዝውውር፣ ሳያስፈልግ ወደ ትንሽ ልጅ የተላኩ ጸያፍ ቁሳቁሶች፣ አሳሳች ልዩ ስሞችን መጥራት፣ አሳሳች ቃላት ወይም ዲጂታል በይነመረብ ላይ ምስሎችን መለጠፍ የመሣሰሉትን ጥርጣሬዎች ሪፖርት ማድረጊያ 24/7 ክፍት መስመር።

ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ የስልክ መስመር
Safe Schools Maryland Hotline . . . 833-MD-B-Safe (833-632-7233)
የ 24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስለ ክስተቶች መረጃ ሪፖርት ሲደረግ የደዋዩን ስም -ሳይገለጽ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ለሚመለከታቸው ቢሮዎች ይደርሳል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (24 ሰዓት) 240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
የተጠረጠረን የሕፃናት በደል ወይም ቸልተኝነት ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር ክፍት ይሆናል።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎቶች 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የጎልማሶችን መበደል እና ቸልተኝነት ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የስልክ መስመር

የሞንትጎምሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ:- 240-773-5400
በልጆች እና በጎልማሶች ላይ የወሲብ ወንጀሎችን፣ በሕጻናትን ላይ አካላዊ በደል መፈጸም፣ ከቤት ሽሽት፣ የጠፉ ልጆችን፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃትን፣ የአዛውንቶችን በደል/ተጋላጭ የአዋቂዎችን በደል፣ እና የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን የፈጸሙ ግለሰቦች የምዝገባ ጥሰቶችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

የሞንንጎምሪ ካውንቲ ፖሊስ :-
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች የጥቆማ መስመር። . . 240-773-ወሮበላ (GANG (4264) ወይም 240-773-አደንዛዥ እፅ (DRUG) (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ህገ -ወጥ የአደንዛዥ ዕፅ/የወንበዴ እንቅስቃሴዎችን መረጃ ማንነትን ሳያሳውቁ ጥቆማ ለመተው 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

### የ MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች 240-740-4692

ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ:- 240-740-3030

የአከባቢ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንቶች፣ የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ 240-740-3100

የአከባቢ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት፣ የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ 240-740-5630

ስለ ሰክሽን 504 ውሳኔ እና አፈጻጸም 240-740-3230

### የሞንትጎመሪ ድንገተኛ ያልሆነ ሪሶርሶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ አስቸኳይ ላልሆነ ጥሪ የስልክ መስመር
301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ውጭ240-777-0311

### የ MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ:- www.montgomeryschoolsmd.org
አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎች ለማግኘት:-

ትዊተር:- MCPS on Twitter . . www.twitter.com/mcps

ትዊተር በስፓንሽኛ:- MCPS en Español www.twitter.com/mcpsespanol

ፌስቡክ:- MCPS on Facebookwww.facebook.com/mcpsmd

ፌስቡክ በስፓንሽኛ:- MCPS en Españolwww.facebook.com/mcpsespanol

የማስጠንቀቂያ መልክቶች:-
Alert MCPSwww.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

## የ MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ ኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች - MCPS QuickNotes Email Messages and Newsletter . . . . www.mcpsQuickNotes.org

የ MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፦
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . .240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

የ MCPS የህዝብ መረጃ ቢሮ 240-740-2837
MCPS Television www.mcpsTV.org;ቴሌቪዥን Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36
በድምፅ የተቀረጸ የአደጋ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . . . . . . . . . .301-279-3673

## የ MCPS ሪሶርሶች ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት፦

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የት/ቤት ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሰራተኞች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ
B The One

ጉልበት መጠቀም፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ጥበብ ትምህርት
Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፕሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች እና የወሮበሎች እንቅስቃሴ

## የ MCPS ሪሶርሶች ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መገለጫ መመሪያ

የምሣ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግምገማዎች

myMCPS Classroom

ፀረ-መድሎ

በኦንላይን የመመረቂያ ፈለግ

የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኖች እና ደንቦች

ስነልቦናዊ አገልግሎቶች

የተማሪ ፐርሶኔል አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና በቸልተኝነት የተተወ ሁኔታን ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ እገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ - Social Media Digital Citizenship

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የፕላን ዝግጅት

የተማሪ የስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ ገመና የመሸፈን መብት

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን መግደል መከላከል

የሰመር ትምህርት

# መግቢያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የማደግና የመበልጸግ ዕድሎችን ለመስጠት ቁርጠኛ ነው የዚህ ቁርጠኝነት አካል የሆነው፥ ተማሪዎቻችን በመማር ላይ የተሰማሩ እና በትምህርት ቤት ማህበረሰብ መካከል ንቁ ተሳታፊ የሆኑበት፣ ትምህርት ቤቶቻችን ከአድልዎ፣ ከጉልበተኝነት፣ ከትንኮሳ እና ከመንቋሸሽ የፀዱ በመሆናቸው ደህንነታቸው የተጠበቀና ተቀባይነት ኖሯቸው የሚማሩበት የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲኖራቸው ማረጋገጥ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ዋና እሴቶች፣ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት፣ እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣  ፀረ-አድሎአዊነት፣ እኩልነት እና ባህላዊ ብቃት ፥ ከሌሎች የግል ባህሪዎች በተጨማሪ የሥርዓተ -ፆታ ማንነትን፣ እንዲሁም ጾታን፣ የሥርዓተ -ፆታ መገለጫ እና የጾታ ዝንባሌን መሠረት በማድረግ የሚደረጉ መድልኦን፣ ማግለልን፣ እና የጉልበተኝነት ተፅእኖዎችን ይከለክላል።

እነዚህ መመሪያዎች ዲስትሪክቱ በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በመመሪያነት የሚያገለግሉ በርካታ የቦርድ ፖሊሲዎችን እና የ MCPS ደንቦችን እንዲሁም የስቴት እና የፌዴራል ሕጎችን በተመለከተ ፈጣን ማጣቀሻ ለመስጠት የታሰቡ ናቸው። እነዚህ መመሪያዎች ሊከሰቱ የሚችሉትን እያንዳንዱን ሁኔታ ዝርዝር አስቀድሞ መገመት አይችሉም። ከዚህም የተነሣ፣ የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎቶች በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በመመስረት  ግምገማ ሊደረግበት ይገባል።

MCPS እነዚህን መመሪያዎች ከ MCCPTA-LGBTQ ንዑስ ኮሚቴ አባላት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አዘጋጅቷል። ይህ መጎዳኘት ለሁሉም ተማሪዎች አክብሮትን እና አድናቆትን ያበረታታሉ፥ እንዲሁም ለትምህርት፣ ለግንኙነቶች፣ ለመከባበር፣ ለትምህርት ልህቀት እና ፍትሃዊነት ያለንን የማህበረሰባችንን ዋና እሴቶች ያጠናክራል። ማህበረሰባችን ለሁሉም ፍትሃዊነትን፥ አካታችነትን፥ እና ተቀባይነትን ለማዳበር እና ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሲሳተፍ ቆይቷል። የዚህ ቁርጠኝነት አካል የእኛ የ LGBTQ ተማሪዎች አብረን በምንማርባቸው ትምህርት ቤቶች ያለ አድልዎ፣ በጉልበተኝነት ወይም በትንኮሳ ምክንያት ሳይሸማቀቁ የጾታ ማንነታቸውን መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው።

ለሁሉም የ MCPS የሥራ ባልደረቦች የሥርዓተ -ፆታ ማንነት ጉዳዮችን ማወቅ እና ማክበር ወሳኝ ነው፤ የሥርዓተ -ፆታ ማንነትን በተመለከተ ለተማሪዎች ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ሁሉንም ምክንያታዊ ማመቻቸቶችን ማድረግ፤ እና የተማሪን ግላዊነት እና ምስጢራዊነት መጠበቅ ተገቢ ነው።

ከተማሪ ጾታ ማንነት አንፃር እነዚህን ግቦች ለማሳካት MCPS የሚከተለውን መመሪያ አዘጋጅቷል።

- የሥርዓተ -ፆታ ማንነታቸውን የሚያረጋግጡ፥ ጾታቸውን የቀየሩ ወይም የጾታ ማንነታቸውን የማያረጋግጡ ተማሪዎችን ጨምሮ በትምህርት ቤት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ድጋፍ ማድረግ።
- ጾታ የቀየሩትን እና የጾታ መለያቸውን የማያረጋግጡ ተማሪዎችን መገለል እና ማግለልን መቀነስ።
- ጾታቸውን የቀየሩትን እና ጾታቸውን የማያሳውቁ ተማሪዎችን ማህበራዊ መስተጋብር እና የአካታችነትን ባህል ማዳበር።
- ተማሪዎች የፆታ ማንነታቸውን ወይም ጾታ የመቀየር ሁኔታን የግል እና ሚስጥራዊ የማድረግ መብታቸውን ማክበር።
- የተማሪ ጾታ ማንነት እና አገላለጽ ጉዳዮችን በአግባብ እና በዘለቄታ ለመፍታት እንዲያስችላቸው ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ባልደረቦች ድጋፍ መስጠት።

እነዚህ መመሪያዎች አጋዥ እንደሚሆኑዎት ተስፋ እናደርጋለን። በዚህ መመሪያ ውስጥ ስለማንኛውም ነገር ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን በመጀመሪያ ከት/ቤት አስተዳዳሪዎችዎ ጋር ይነጋገሩ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዋችሁ፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የዲስትሪክት ስራዎች የተማሪ ደህንነት እና ስምምነት ጽ/ቤት ጋር  240-740-3215 ይደውሉ፣ SWC@mcpsmd.org ወይም TitleIX@mcps.org።  ስለ ተማሪ ጾታ ፈጣን መመሪያ  በተማሪ ደህንነት እና ስነ ሥርዓት ማክበር ሠነድ ላይ ይገኛል። ጥያቄዎን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ሊመለሱ ካልቻሉ፣ የትምህርት ቦርድ የሥራ ሃላፊን ወይም የቦርድ እንባ ጠባቂን በስልክ ቁጥር 240-740-3030 ወይም boe@mcpsmd.org ማግኘት ይችላሉ።

## ■ ትርጉም

እዚህ ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች ልውጥ ጾታ እና ጾታቸውን መግለጽ ያልቻሉ ተማሪዎችን ለመደገፍ እንጂ ተማሪዎችን ለመፈረጅ ታስቦ አይደለም። ተማሪዎች እራሳቸውን ለመግለጽ እነዚህን ቃሎች ሊጠቀሙ ወይም ላይጠቀሙ ይችላሉ።[3፣4]

**AGENDER (ከየትኛውም ጾታ ያልሆኑ)** **የጾታ መገለጫ የሌላቸው (እንዲሁም "ያለጾታ" ወይም "ጾታ የሌለው") ።**

**የተወለደ(ች)በት ጾታ ስያሜ/CISGENDER**የጾታ ማንነት እና የጾታ አገላለጽ የተወለደ(ች)በትን የጾታ ስያሜ የያዘ/ች ሰው፣ ጾታ ያልቀየረ/ች ሰው ወይም ሥርዓተ-ፆታ የማያሟላ/የማታሟላ(የማያረጋግጥ/የማታረጋግጥ) ሰው ።

**የጾታ አገላለጽ የአንድ ሰው የጾታ ውክልና ወይም ለሌሎች አገላለጽ፣** በአብዛኛው በባህርይ፣ አለባበስ፣ የጸጉር አያያዝ ዘይቤ፣ እንቅስቃሴዎች፣ ድምፅ፣ ንግግር እና የቃላት አመራረጦች፣ ወይም ለየት ያለ የአነጋገር ዘይቤዎች።

**ጾታቸውን በመግለጽ የሚወላውሉ-GENDER FLUID** የጾታ ማንነቱ(ቷ) ወይም የጾታ መገለጫ(ዋ) ቋሚ ያልሆነ እና እንደየሁኔታው የሚቀያይር-የምትቀያይር ሰው።

**የሥርዓተ -ፆታ ማንነት አንድ ሰው በጥልቅ የያዘው-የያዘችው ውስጣዊ ስሜት ወይም የግለሰብ ጾታ ሥነ ልቦናዊ ዕውቀት።** የአንድ ሰው የጾታ መገለጫ በትውልድ ከተሰጠው/ከተሰጣት የጾታ ማንነት ጋር አንድ ዓይነት ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች በተወለዱ ጊዜ ከተሰየሙት የጾታ መለያ/ማንነት ጋር የሚገጣጠም የጾታ መገለጫ አላቸው። ቢሆንም እንኳ፣ ለአንዳንዶች፣ የፆታ ማንነታቸው በተወለዱበት ጊዜ ከተሰየመላቸው የፆታ መለያ የተለየ ነው። ጾታቸውን የቀየሩ ወይም ጾታቸውን የማያረጋግጡ/የማይገልጹ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰዎች ሁሉ የጾታ ማንነት አላቸው። ለዚህ መመሪያ ዓላማ፣ የአንድ ተማሪ ፆታው(ዋ) በት/ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ በይፋ የታወቀ/የተረጋገጠው ነው።

**GENDER NONCONFORMING/ሥርዓተ -ፆታ የማያሟሉ** በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ካለው/ከተለመደው/ባህላዊ ከሆነው የተለየ አገላለጽ ወይም የተወሰነ ወይም "አነስታይ/feminine" ወንዶች፣ "ተባታይ/masculine" ልጃገረዶች፣ የማይለወጥ አመለካከት የመሣሠሉ እና ጾታዊ አገላለጻቸው አንድሮጅነስ/androgynous/ከፊል ወንድ ከፊል ሴት የሆነ/ች። ይህ የሚያካትተው በተለምዶ ከሚታወቀው ዓይነት የፆታ አገላለጽ ስያሜ ውጪ ወይም እንደ ሁለት ወይም የበለጠ (የተለየ) ፆታዊ ማንነት እንዳላቸው የሚገልፁትን ነው። ሌሎች ተመሳሳይ ትርጓሜዎች ሊኖራቸው የሚችሉ ቃላት የሚያካትቱት "የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት/ልዩ ልዩ ፆታ" ወይም "ጾታን የሚያራምዱ/የሚያስፋፉ" ናቸው።

**ወንዳገረድ/INTERSEX** ወንድ ወይም ሴት ተብሎ ከሚገለፀው መደበኛ የጾታ አገላለጽ ጋር የማይገጥም አካላዊ ወሲባዊ/ጾታዊ ባህሪያት ከማሳደግ ጋር የተያያዙ በርካታ ሁኔታዎች።

**LGBTQ ምህጻረቃል** ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ወንዳገረድ፣ ጾታ የቀየረ(ች)/ትራንስጀንደር፣ ኩዌር/ተባእት-እንስት ያልሆነ፣ እና ማህበረሰብ ጠያቂ። ይህ ምህፃረ ቃል ብዙውን ጊዜ ሁሉን ያካተተ ለማድረግ ሲባል LGBTQ + ተብሎ ይጻፋል። የተለየ ጾታ የሌላቸውን/asexual ጭምር ለማካተት ሲባል "LGBTA ወይም LGBTI" ተብሎም ይገለጻል፣ "I" የሚወክለው ሁለቱንም የጾታ መገለጫ ያላቸውን፣ ወይም ከላይ የተገለጹትን በሙሉ እንዲወክል " LGBTQIA" ይባላል።

**ከሁለቱም ያልሆነ** ወንድ ወይም ሴት አድርጎ የማይለይ፣ ወይም በጭራሽ ጾታ የማይለይ ሰው። ጥቂት ከተለምዶአዊ ጾታ የሚለዩ ሰዎች ጾታቸውን የቀየሩ ናቸው።

**በመወለጃ ጊዜ የተሰየመ ጾታ በህፃንነት የልደት ሠርተፊኬት ላይ የተሰየመ ጾታ፣ በልደት ቀን/በተወለዱበት ቀን እንዲህ ዓይነት ሰነድ/ምዝገባ መሰጠት አለበት።**

**ጾታዊ መግለጫ** የአንድን ሰው ስሜታዊ፣ የፍቅር ግንኙነት፣ ወይም ለሌላ ሰው የፍቅር ዝንባሌን ይገልጻል። አንዳንድ የጾታ ዝንባሌ ምሳሌዎች፡- ጌይ/ከወንድ መሰል ጾታ ጋር ዝንባሌ ያለው/ግብረ ሰዶማዊ፣ ሌዝቢያን/ከሴት መሰል ጾታ ጋር ዝንባሌ ያላት፣ ወንዳገረድ/ከአንድ ጾታ ጋር ብቻ ሳይሆን ከየትኛውም ጾታ ጋር ዝንባሌ ያለው-ያላት (BISEXUAL)፣ ለማንኛውም ጾታ ዝንባሌ የሌለው-የሌላት (ASEXUAL)፣ ወይም ተፈጥሮአዊ የጾታ ውስንነት ዝንባሌ የሌለው-የሌላት (PANSEXUAL) ናቸው።

**የጾታ ለውጥ የአንድ ሰው የጾታ ማንነት ወይም መገለጫ ከተለመደው በተወለደ/ች ጊዜ ከተሰየመ ጾታ የተለየ ቅጽላዊ አገላለጽ ነው።** ተመሣሣይ ትርጉም የሚኖራቸው ሌሎች ቃሎች " ቅይር ሴት/ወንድ transsexual (ሴት ነኝ ብሎ የሚያምን ወንድ/ወንድ ነኝ ብላ የምታምን ሴት-- በቀዶ ጥገና ፆታውን ያስቀየረ/ያስቀየረች) " እና " ቅይር/trans "

**TRANSITION** ሰው በተወለደ(ች)በት ጊዜ ከተሰጠው/ከተሰጣት ጾታ ይልቅ፣ ራሱ(ሷ) በሚሰይመው/በምትሰይመው ጾታ ለመኖር የሚወስንበት ሂደት ጾታቸውን የቀየሩ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች የጾታ ምንነታቸውን በይፋ ለመግለጽ፣ የተለያዩ እርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ (ለምሳሌ፡- ቅጥያ ስም መጠቀም ወይም በህጋዊ ሠነዶቻቸው ላይ ስማቸውን እና/ወይም ጾታቸውን በህጋዊነት መቀየር፣ የልብስ አመራረጥ እና የጸጉር አሠራርን ጾታቸውን በሚያንፀባርቅ መልኩ መሥራት፣ እና በአጠቃላይ አኗኗራቸው፣ እና ራሳቸውን ለሌሎች የሚያቀርቡበት አኳኋን ፆታቸውን ገላጭ ይሆናል)። ጥቂቶች፣ ነገር ግን ሁሉም አይሆኑም፣ ፆታቸውን የሚቀይሩ ሰዎች እድገ-ንጥር/ሆርሞን/ መድኃኒት ይወስዳሉ ወይም በቀዶ ጥገና ህክምና ተለውጦ ሰውነታቸው ከፆታ ማንነታቸው ጋር እንዲመሣሰል ያስደርጋሉ። ምንም እንኳን ሽግግር የአንድን ሰው የሥርዓተ -ፆታ ማንነት ሕዝባዊ አገላለጽ የሚያካትት ቢሆንም፣ ሽግግር የግል ሂደት ሲሆን ሽግግር ያላቸው ግለሰቦች የግላዊነት መብት አላቸው።

**X MARKER**ለወንድ "M" ወይም ለሴት "F" የሥርዓተ -ፆታ አመልካች ምድቦችን የማይለይ ሰው

---

[1]ተዛማጅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን እና የ MCPS ደንቦች/Related Montgomery County Board of Education Policies and MCPS Regulations፡- ACA, ACF, JHF, JHF-RA, ACA-RA, ACF-RA, COA, COA-RA

[2]የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት እና የተጨማሪ መገልገያዎችን ዝርዝር ለማወቅ .. ይመልከቱ፡- የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ጾታ የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን ላላሟሉ ወጣቶች ሰላማዊ/የማያሰጋ ስፍራ ማዘጋጀት/መስጠት፡-

ስለ ሥርዓተ-ፆታ ማንነት ያለማዳላት መመሪያ (ኦክቶበር 2015)፥ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፡- marylandpublicschools.org/about/Documents/DSFSS/SSSP/ProvidingSafeSpacesTransgendergenderNonConformingYouth012016.pdf.

[3] በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጸው ሃረግ በተቻለ መጠን ሁሉን ያካተተ እንዲሆን የታሰበ ነው፣ ቢሆንም ግን፣ ሃረጎቹ እና ቋንቋ ቀስበቀስ የሚያድግ እና ቶሎ ወቅት የሚያልፍበት/የሚያረጅ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ፍቺ/ትርጉሞቹ የተሰጡት ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ምንጮች ነው፡- American Civil Liberties Union; American Psychological Association; Baltimore City Schools; California School Boards Association; Chicago Public Schools; District of Columbia Public Schools; Gay, Lesbian, and Straight Education Network; Howard County Public Schools; Human Rights Campaign; Lambda Legal; Maryland State Department of Education; Maryland Public Secondary Schools Athletic Association; Massachusetts Department of Elementary and Secondary Education; National Collegiate Athletic Association; National School Boards Association; New York City Department of Education; PFLAG; and Trevor Project.

## ፆታ ከቀየሩ እና ፆታቸውን ከማይገልጹ ተማሪዎች ጋር በቀዳሚነት/Proactively አብሮ መሥራት

### የሥርዓተ -ፆታ ድጋፍ ዕቅድ

ርእሰመምህር (ተወካይ)፣ ከተማሪዎች እና ከወላጆቻቸው/ቤተሰቦቻቸዉ ጋር በመተባበር (ቤተሰቡ ተማሪው(ዋ)ን የሚደግፉ ከሆነ)፣ በት/ቤት ጠቅላላ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ በእኩል የመሣተፍ እድል እንዲኖራቸው እና በት/ቤት ጾታን መሠረት -ያደረገ አድሎአዊነት ለመከላከል የሚያስችል እቅድ/ፕላን ማዘጋጀት አለባቸው። ርዕሰ መምህር፣ ተወካይ ወይም የት/ቤት-የአእምሮ ጤና ባለሙያ (ለምሳሌ፡- የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያ፣ የትምህርት ቤት ካውንስለር፣ እና/ወይም የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ) መጠቀም ያለበ(ባ)ት የ MCPS ቅጽ 560-80 የመቀበያ ቅጽ፡- ለተማሪዎች የጾታ መለያ ድጋፍ መስጠት ይህንን ሂደት መደገፍ፣ ተማሪ በትምህርት ቤት ተሳታፊ እንዲሆን-እንድትሆን መደገፍ ነው። የተሞላው ቅጽ በተማሪ ፋይል ማጠራቀሚያ ወይም ሚስጥራዊ ፋይሎች ላይ ሳይሆን አስተማማኝ በሆነ ስፍራ መቀመጥ አለበት። እቅዱ/ፕላኑ በሁሉም የት/ቤት ባልደረቦች በትክክል/በቋሚነት የሚተገበር ቢሆንም ቅጹ ራሱ በሌሎች የት/ቤት ባልደረቦች መታየት ወይም ሊጠቀሙበት አይገባም።

- የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት እንደ ጉዳዩ ሁኔታ አንድ-በአንድ መገምገም አለበት፣ እና ሁሉም እቅድ በሂደት እየተገመገመ እንደአስፈላጊነቱ ይከለሳል። የእቅዱ አካል እንደመሆኑ፣ ትምህርት ቤቶች ከተማሪው(ዋ) ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሚኖራቸውን የሥራ ባልደረቦች መለየት አለባቸው። እንዴት ድጋፍ እንደሚሰጥ፣ እንዴትና ለማን ኢንፎርሜሽን መነገር እንዳለበት በእቅዱ ላይ መገለጽ/መታየት/መነደፍ አለበት።
- በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ እቅድ ይፋዊ ስም፣ ተውላጠ ስሞች፣ አትሌቲክስ፣ ከቀለም ትምህርት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎችን፣ ሎከር ክፍሎችን፣ የመጸዳጃ ክፍሎችን፣ ሠላማዊ ቦታዎችን፣ ሠላማዊ ቀጣናዎችን፣ እና ሌላ ሠላማዊ ድጋፎችን፣ እና ምረቃ የመሣሠሉ ይፋዊ ሁነቶችን እንደሚከወን መገለጽ አለበት።

### ከቤተሰብ ጋር መግባባት

ርእሰ መምህሩ/ሯ ወይም የተመደበው/ችዉ ግለሰብ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር ከመነጋገራቸው አስቀድመው፣ ከቤት ምን ያህል ድጋፍ እንዳለው/እንዳላት ወይም ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚጠብቅ/እንደምትጠብቅ ለማረጋገጥ ከተማሪው(ዋ) ጋር መነጋገር አለባቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን ይፋ የማያደርጉ ተማሪዎች ስለደህንነታቸው በመስጋት ወይም ተቀባይነት ስለማይኖር ቤት ውስጥ በገሃድ ስለጾታቸው አይናገሩም ይሆናል። የጾታ ማንነት መለያ ጉዳዮች ውስብስብ እና ቤተሰባዊ አለመግባባትን ሊያስከትል ይችላል። ጉዳዩ ይህ ከሆነ እና ድጋፍ የሚያስፈልግ ከሆነ፥ የተማሪ ደህንነት እና ስነ ሥርዓት አስከባሪ (SWC) ማነጋገር ያስፈልጋል። በዚህ ሁኔታ፣ ሠራተኞች ቤተሰብን የሚያካትት፣ ከተቻለ፣ የሠላም ስጋቶችን፣ እና የተማሪ ግላዊ ገመናን ግምት ውስጥ ማስገባት፣ እና የቤተሰብ ድጋፍ ባይኖርም እንኳ ለተማሪ ድጋፍ መስጠት በጣም አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ተማሪ-መር እቅድ ይደግፋሉ።

## መረጃ/ኢንፎርሜሽን ይፋ ማድረግ እና ግላዊነት

- ሁሉም ተማሪዎች ስለግል ገመናቸው መብት አላቸው። ይህ የጾታ ለውጥ ያደረጉ ወይም ጾታ የማይገልጹትን ግላዊ አቋም በት/ቤት ገመና የመጠበቅ መብትን ያካትታል።
- ስለ አንድ ተማሪ የፆታ መቀየር አቋም፣ ህጋዊ ስም፣ ወይም በተወለደ(ች) ጊዜ የተሰጠ ፆታ ከህክምና ጋር የሚገናኝ ሚስጥራዊ መረጃ ሊሆን ይችላል። ይህንን መረጃ ለሌሎች ተማሪዎች፣ ለእነርሱ ቤተሰቦች/ሞግዚቶች፣ ወይም ለሦስተኛ ወገኖች ይፋ ማድረግ፣ ስለ ግላዊ ገመና እንደ ፌደራል Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA) የመሣሰሉ ህግጋትን መጣስ ይሆናል።
- በስቴት፣ የአካባቢ፣ እና የፌደራል የግላዊ ገመና አጠባበቅ ህጎች መሠረት፣ ጾታ የቀየሩትን ጭምር የተማሪዎች የህክምና መረጃዎችን በሙሉ በሚስጥር መጠበቃቸውን ትምህርት ቤቶች ያረጋግጣሉ።
- ስለ ጾታ አቀራረብ፣ ማንነት፣ እና ብዙሃነትን/ልዩነትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ ለት/ቤት የሃኪም ምርመራ፣ ህክምና፣ እና/ወይም ሌሎች ሠነዶች አስፈላጊ ያለመሆናቸዉን እባክዎ ይገንዘቡ።
- ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን ያልገለጹ ተማሪዎች ስለ ጾታ ማንነታቸው ለመወያየት እና የጾታ ምንነታቸውን በግልጽ ለማረጋገጥ እና መቼ፣ ከማን ጋር፣ እና ምን ያክል ግላዊ ገበናን መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመለዋወጥ የመወሰን መብት አላቸው። ተማሪዎች አቋማቸውን ለሥራ ባልደረቦች ወይም ለሌሎች ተማሪዎች መግለጻቸው ማለት የትምህርት ቤት የሥራ ባልደረቦች የተማሪን አቋም ለሌሎች፣ ወላጆችን/ሞግዚቶችን እና ሌላ የትምህርት ቤት ባልደረቦችን ጭምር በህጋዊነት እንዲያደርጉት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ወይም ተማሪዎቹ ተስማምተውበት ካልሆነ በስተቀር ከተማሪ የተገለጸላቸውን አቋም ይፋ የማድረግ ስልጣን የላቸውም።
- ጾታ የቀየሩትን ወይም ጾታቸውን ያላረጋገጡ ተማሪዎችን በት/ቤት ድጋፍ ለመስጠት አስፈላጊ ከሚሆነው የበለጠ በርካታ ጥያቄዎችን መጠየቅ አግባብ አይደለም።

## ስሞች/ተውላጠ ስሞች

ሁሉም ተማሪዎች በመረጡት ስም እና/ወይም ተውላጠ ስም የመጠራት መብት አላቸው። የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ከተገለጸው ስም እና ተውላጠ ስም ከፆታ መገለጫቸው ጋር በማስማማት መጥራት አለባቸው። ተማሪዎች በራሳቸው ተለይተው ከተመረጡ ስሞች ጋር በሚዛመዱ ስም እና ተውላጠ ስም ለመጠራት ከታች በተጠቀሰው ክፍል በተገለፀው መሰረት እንደ ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ ቋሚ የተማሪ ሪከርዶቻቸውን መቀየር እይጠበቅባቸውም (ለምሳሌ፡- በፍርድ ቤት-የታዘዘ ስም እና/ወይም አዲስ የልደት ሰርተፍኬት)። በተቻለ መጠን፣ እና ከእነዚህ መመሪያዎች ጋር በማይጣረስ መልኩ፣ የተማሪ የጾታ መቀየር ሁኔታ በምስጢር እንዲጠበቅ የትምህርት ቤት ስራ ባልደረቦች ጥረት ያደርጋሉ።

### የሰራተኞች ግንኙነት

ትምህርት ቤቶች የተማሪ ው(ዋ)ን በተወለደ(ች)በት ወቅት የተሰየመ የጾታ መለያ እና ህጋዊ ስም በትምህርት ሪኮርዶች እና ሌሎች ሠነዶች ላይ መጠቀም ህጋዊ ግዴታ እስካልሆነ ድረስ፣ ትምህርት ቤት በተማሪው(ዋ) አማካይነት የተገለጸውን ስም እና ጾታ በመማርያ ክፍል መዝገቦች (rosters)፣ በመታወቂያ መለያ፣ በማስታወቂያዎች፣ በሠርተፊኬቶች፣ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ እና በዓመታዊ መጽሔቶች ላይ መጠቀም አለባቸው። የተዛባ ጾታዊ አገላለጽን ወይም የስም አጠራር ግድፈትን ጎጂነት ለማስወገድ፣ በተለይም ትምህርት ቤቶች ጥንቃቄ ማድረግ የሚኖርባቸው ከሁሉም ተተኪ አስተማሪዎች ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ከተማሪው(ዋ) የተገለጸ ስም እና ጾታ ጋር ተመሣሣይ መሆኑን በማረጋገጥ ነው።

- ትምህርት ቤቶች የተማሪን ጾታ የሚገልጹ ወይም እንደ ወንዶች/ልጃገረዶች (ተማሪዎች በማለት ፈንታ) ወይም እናት/አባት (ወላጅ/ሞግዚት በማለት ፈንታ) ስለጾታ ገላጭ በሆኑ ቃላት የፈቃድ መስጫ ወረቀቶችን እና ሌሎች የትምህርት ቤት- ቅጾችን አጠቃቀም መቀነስ ይኖርባቸዋል።
- በተማሪ ወይም በወላጅ/ሞግዚት ተለይቶ የተገለጸ ካልሆነ በስተቀር፣ የጾታ ለውጥ ያደረገ/ች ተማሪን ወላጅ/ሞግዚት መገናኘት ሲያስፈልግ፣ የ MCPS ት/ቤት ሠራተኞች ተማሪው(ዋ) በተወለደ(ች)በት ወቅት ከተሰጠው/ከተሰጣት ስያሜ ላይ ያለውን ህጋዊ ስም እና የተውላጠ ስም መጠቀም አለባቸው።
- ስለ አስንድ ሰው ተውላጠ ስሞች መጠየቅ ጾታ ለቀየሩ፣ ጾታቸውን ለማይገልጹ፣ እና ከሁለቱም ጾታ ያልሆኑትን ይበልጥ አካታች እና አመቺነት ይፈጥራል።

## ቋሚ የት/ቤት ሪከርዶች

ት/ቤቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ ቋሚ የሆነ ፋይል/መዝገብ ሊኖራቸው ይገባል፣ ይሄም የተማሪን ፆታ እና ህጋዊ ስም ማካተት አለበት። የተማሪን ጾታ ወይም ህጋዊ ስም መቀየር የሚፈልጉ ተማሪዎች ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች ከት/ቤት ካውንስለር ጋር መማከር አለባቸው፣ ይሄውም ባለሙያ ቅጹን በመሙላት ቤተሰብን የሚረዳበት ቅፅ 560-80፣ የመቀበያ ቅፅ፡-ነው። የተማሪ ጾታ ማንነትን መደገፍ፣ እና ማንኛውንም ጥያቄዎች ወደ ተማሪ ደህንነት እና የሥነ ሥርዓት ተገዢነት ማስተላለፍ። የተማሪ ጾታ እና ህጋዊ ስም ላይ የሚደረጉ ለውጦች የሚታዩት በተለየ የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE) መስፈርቶች ነው። ለተጨማሪ መረጃ፣ MCPS ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ ሪኮርዶችይመልከቱ።

ህጋዊ ስም ላይ የሚደረግ ለውጥ፡- የተማሪ ህጋዊ ስም መለወጡን የሚገልጽ ሠነድ ሲቀርብ ይህንኑ የተማሪ ህጋዊ ስም መለወጡን ለማንፀባረቅ የተማሪ ቋሚ ሪኮርድ ይለወጣል። ከሚከተሉት ሠነዶች/ዶኩመንቶች የትኛውም የህጋዊ ስም ለውጥ ማስረጃ ይሆናል፡-

- የልደት ሠርተፊኬት
- ፓስፖርት/ቪዛ
- የሃኪም ሠርተፊኬት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
- የሆስፒታል ሠርተፊኬት
- የወላጅ/የአሳዳጊ ቃለ መሀላ
- ሲወለድ/ስትወለድ የተመዘገበ(ች)በት
- ሌላ የልደት ሰርተፍኬት ማረጋገጫ

አንድ ተማሪ እና/ወይም የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ በተማሪው(ዋ) ቋሚ መዝገብ ላይ ለውጥ እንዲደረግ ከጠየቀ(ች)፣ እንደዚህ ያለ ሰነድ ከሌለ፥ ትምህርት ቤቱ SWC ማነጋገር አለበት።

የፆታ ለውጥ፡- የተማሪ ፆታ የግል-መግለጫ/መለያ ለተማሪ ቋሚ ሪከርድ በቂ ነው። በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE) መመሪያ መሰረት፣ የተማሪ ሪከርዶች ተማሪን ወንድ፣ ሴት ወይም ፆታ X ብለው ሊለዩ ይችላሉ። የሜሪላንድ ተማሪ ሪከርዶች ስርዓት መመሪያ የተማሪ ፆታ የግል-መግለጫ/መለያ በተማሪ ሪከርዶች ላይ የሚፈቅደው በሚከተለው መሰረት ነው፡-

1-ወንድ

2-ሴት

X-ከሁለቱም ጾታ-ያልሆነ (X-Non-Binary)፣ ተማሪ ወንድ ወይም ሴት ወይም ሁለቱም ጋር ራስን አለመመደብ

ይፋ ማድረግን መከላከል፡- በተማሪ ጾታ እና/ወይም ህጋዊ ስም ለውጥ ከተደረገም በኋላ ት/ቤቱ የቀድሞውን የተማሪ ማንነት መጠበቅ አለበት። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን የተማሪ ሪኮርድ ጥበቃ መመሪያ፥ Office of Shared Accountability (OSA) ወይም SWC ይመልከቱ።

ትምህርት ቤቶች ለመደበኛ ፈተናዎች ወይም ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) ሪፖርቶች ለመሳሰሉ ከተማሪ ቋሚ ሪኮርዶች ላይ የሚገኙ ጾታ እና ህጋዊ ስሞችን እንዲጠቀሙ በሚያስፈልግበት ወቅት፣ የትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች እና አስተዳዳሪዎች የተማሪ ጾታን እና ህጋዊ ስምን ይፋ በማድረግ ሆን ተብሎ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው ከተማሪው(ዋ) መለያ ስምና ጾታ የተለየ በሚሆንበት ጊዜ ነው።

ቋሚ የት/ቤት ሪከርድ ላይ የጾታ እና/ወይም የስም ለውጥ ሲደረግ—

- ለ MSDE ተገቢ ማሳወቂያ እንዲደረግ ት/ቤቱ ለ OSA ማሳወቅ አለበት፤
- የት/ቤት አስተዳደሮች ቤተሰቦች ከውጪ (ለምሳሌ፡- የክትባት ሪከርዶች፣ የዶክተር ትዕዛዞች፣ ወይም ከህክምና ሌላ ሪከርዶች) የማንኛውም ሪከርዶች ማሻሻያ የተደረገበት ግልባጭ ለት/ቤት እንዲያቀርቡ መምከር አለባቸው።

የቀድሞ ተማሪዎች፡- በተመሳሳይ መልኩ፣ የቀድሞ ተማሪ ቋሚ ሪከርድ መቀየር ያለበት የቀድሞ ተማሪ ጾታ እና/ወይም ህጋዊ ስም ላይ የተደረገ ለውጥን ለማንፀባረቅ ነው፣ ይሄም የሚሆነው ጾታ እና/ወይም ህጋዊ ስም መለወጡን የሚያሳይ ሰነድ በተቀበለ ጊዜ ነው። እነዚህ ለውጦች የሚከናወኑት በማእከላዊ ሪኮርዶች/መረጃ ነው።

## የአለባበስ ደንብ/ሥርዓት

- ጾታ የቀየሩ ወይም ጾታቸውን የማይገልጹ/የማያረጋግጡ ተማሪዎች የ MCPS የአለባበስ ኮድ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ፣ የጾታ ማንነታቸውን ወይም ጾታቸውን ገላጭ የሆነ አለባበስ የመልበስ መብት አላቸው። የትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች ጾታ በቀየሩ ወይም ጾታቸውን ለይተው ያላሳወቁ/የማያረጋግጡ ተማሪዎች ላይ ስለ አለባበስ ኮድ በሌሎቹ ተማሪዎች ላይ ከሚያደርጉት የተለየ ጫና ማድረግ አይኖርባቸውም።
- ትምህርት ቤቶች ለመማሪያ ክፍል ወይም ለዓመታዊ መጽሔት ፎተግራፎች፣ ለሆነር ሶሳይቲ ሁነቶች፣ ለምረቃ ሁነቶች፣ ወይም ለዳንሶች ጾታን ያላማከለ የአለባበስ ኮድን ግንዛቤ መስጠት አለባቸው። በተጨማሪም፤ በጾታ የተለየ ልብስ በሚለበሱበት ሁኔታዎች (ለምሳሌ፡- በትእይንቶች እና ትርኢቶች ጊዜያት)፣ ተማሪዎች ከጾታ መገለጫቸው ጋር የሚስማማ ልብስ እንዲለብሱ መፈቀድ አለበት።

## በጾታ ላይ የተመሰረቱ ተግባሮች

- ት/ቤቶች በጠቅላላ በጾታ ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ እና አፈጻጸሞችን መገምገም ይኖርባቸዋል፣ እና ከትምህርታዊ ዓላማ ጋር የሚስማሙትን ብቻ መጠበቅ አለባቸው። ለምሳሌ፡- የሙዚቃ እና የውዝዋዜ ቡድኖች ተማሪዎችን በተለያዩ ክፍሎች የሚመድቡ ከሆነ፣ በጾታ ከመከፋፈል ይልቅ በድምፅ አይነት/ጥራት ቢመድቧቸው ይሻላል።
- በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም ሌሎች ህጋዊ በሆነ ጾታ-ተኮር ህግ፣ ፖሊሲ፣ ወይም አፈጻጸሞች፣ ተማሪዎች በጾታ በሚለዩበት ማናቸውም ጊዜ ተማሪዎች ከጾታ ማንነታቸው ጋር የሚጣጣም ተሳትፎ እንዲያደርጉ መፈቀድ አለበት።

## በጾታ የተለዩ አካባቢዎች

- መገልገያዎች በፆታ ተለይተው ለተማሪዎች ሲመደቡበፆታ ተለይቶ የሚመደብ መገልገያዎችን እንዲጠቀሙ (ለምሳሌ፡- መፀዳጃ ቤቶች፣ እቃ መቆለፊያ ክፍሎች፣ እና ልብስ መቀየሪያ ክፍሎች) ከተረጋገጠው ፆታ መለያቸው ጋር የሚጣጣም በሆነ መልኩ መሰጠት አለበት።
- በደህንነት ስጋት፣ የግል ሁኔታ፣ ወይም በሌላ ምክንያት የጋራ መገልገያዎችን ለመጠቀም ምቾት ከማይሰማው-ከማይሰማት ማንኛውም ተማሪ ጥያቄ የሚቀርብ ከሆነ፣ የተናጠል መፀዳጃ ክፍል ወይም የመቆለፊያ ክፍሎች፣ በመልበሻ አካባቢዎች ተከልለው የሚጠቀሙበት መጋረጃ፣ በአቅራቢያ የሚገኝ የግል መፀዳጃ ክፍል ወይም ቢሮ መጠቀም፣ ወይም የተለያየ የመቀየሪያ ጊዜ-ሠሌዳ እንዲደረግ እና ሠላማዊ እና ሃፍረትና መሸማቀቅ በማይሰማቸው ሁኔታ መጠቀም የሚያስችላቸው አማራጭ መሰናዶ ሊደረግላቸው ይገባል። ተማሪው/ዋ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መደረግ ያለበት ሚስጥራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።
- በፆታ አምሳያነት ካላቸው ተማሪዎች ጋር በጋራ ለመጠቀም ለሚችሉ ተማሪዎች ሌላ አማራጭ እንዲዘጋጅላቸው አያስፈልግም። አማራጭ ሁኔታ ለመጠቀም በተማሪው/ዋ ጥያቄና የጾታ ለውጥ ያደረገ/ች ተማሪን ግላዊ ሚስጥር ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ ነው።
- አንዳንድ ተማሪዎች በፆታ ተለይቶ የተመደበ መገልገያ ፆታው(ዋ)ን ከቀየረ/ች ተማሪ ጋር ለመጠቀም አይመቻቸውም ይሆናል። ይሄ ያለመመቸት ፆታው(ዋ)ን ለቀየረ/ች ተማሪ እንዳይ(ት)ጠቀምበት ለመከልከል ምክንያት ሊሆን አይችልም። ስለ ጾታ ማንነት ግንዛቤ እንዲኖር እና የሁሉንም ተማሪዎች ባህልና ወግ ማክበርን ለማዳበር ተማሪዎች ያልተመቻቸውን ሁኔታ ለማስተካከል የት/ቤት አስተዳዳሪዎች እና ካውንስል የሚያደርጉ የሥራ ባልደረቦች ከተማሪዎች ጋር መሥራት አለባቸው።

## አዲስ ግንባታ/እድሳት

- አሁን ባሉት ፋሲሊቲዎች የትምህርት ቤት አስተዳደር ለተማሪዎች የጾታ-ገለልተኛ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸው ቁመና ከሌላቸው፣ ትምህርት ቤቶች አሁን የሚገኙትን ፋሲሊቲዎች በማደስ-በማሻሻል ተፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ ከ"Department of Facilities Management" ጋር መሥራት አለባቸው።
- ለተማሪዎች ሠላም/ደህንነት ግንዛቤ በመስጠት፣ የመገልገያዎች አስተዳደር ዲፓርትመንት ጾታ-ገለልተኛ የሆነ መጸዳጃ ለተማሪ/ለህዝብ መጠቀሚያ ንድፍ/ዲዛይን ማዘጋጀት አለበት።
- አስፈላጊነቱ ከታመነበት፣ MCPS በእያንዳንዱ ደረጃ-ፎቅ/ፍሎር እና ሰው በሚበዛበት አካባቢ ቢያንስ አንድ ፆታ-ገለልተኛ ሽንት ቤት መስራት አለበት።
- በተቻለ መጠን፣ MCPS ቢያንስ አንድ ጾታ-ገለልተኝነት ያለው የአልባሳት መቀየሪያ በአዲሶቹ ት/ቤቶች እና የት/ቤት እድሳት ዲዛይኖች ላይ ማካተት ያለበት ሲሆን፣ ጾታ-ገለልተኛ የሆነ መገልገያ ዲዛይን ሲዘጋጅ ለደህንነት የማያሰጋ ሠላማዊ እና ገበናን ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑ በዲዛይኑ እና በቦታ አመራረጡ ግንዛቤ ዉስጥ መግባት አለበት።

## የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት እና በት/ቤቶች ውስጥ የሚካሄድ ስፖርት

- ምንጊዜም ት/ቤት በጾታ-የተለየ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት ሲሰጥ እና በት/ቤቶች ውስጥ ባሉ ስፖርቶች፣ ተማሪዎች ከፆታ መለያቸው ጋር በሚመጥን ስፖርት እንዲሳተፉ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

## በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ

- ትራንስጀንደር እና ጾታ የማያረጋግጥ የተማሪ ተሳትፎ በ MCPS አትሌቲክስ በሜሪላንድ የሕዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር (MPSSAA) ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች (በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል)www.mpssaa.org/assets/1/6/MPSSAA_Transgender_Guidance_revised_8.16.pdf
- በ MPSSAA መመሪያ እና ተወዳዳሪ ፍትሃዊነትን፣ የሴቶች ስፖርቶችን አስፈላጊነትና ያለ አድልዎ ለመሳተፍ የተሟላ እኩል ዕድሎችን መስጠት፣ በ MCPS ውስጥ ትራንስጀንደር እና ጾታ የማይለዩ ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች መካከል የሚደረግ አትሌቲክስ ቡድን ውስጥ እንዲሳተፉ ይፈቀድላቸዋል—
  - ተማሪ በተወለደ(ች)በት ወቅት የተሰጠ የጾታ ስያሜ፤ ወይም
  - ተማሪው(ዋ) ያስለወጠ(ች)ው ጾታ፣ ወይም
  - በተማሪው(ዋ) የተረጋገጠ የጾታ ማንነት።
- በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ ለመሳተፍ ብቁነትን በተመለከተ ማንኛውንም ይግባኝ ወደ MCPS አትሌቲክስ ክፍል ማመልከት አለባቸው።
- በሌሎች ት/ቤቶች የሚደረግ ውድድር፡- በተማሪ ስምምነት እና የተማሪው(ዋ) አገልግሎት አካል ተደርጎ በአካባቢ ት/ቤት የሚሰጠው አይነት መገልገያ በሌሎችም መገልገያዎች/facilities እንዲኖር መደረግ አለበት። ኮች/አሰልጣኝ ወይም ተማሪው/ዋ የሚ(ምት) ማርበት ት/ቤት በሌላኛው በሚጎበኘዉ ት/ቤት ስለ ማንኛዉ ም አስፈላጊ ነገሮች፣ የተማሪው/ዋ ማንነት በሚስጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ማሳወቅ አለበት/አለባት።

## ክለቦች

- ብዙ የ MCPS መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ LGBTQ ን እና የጾታ ምንነትን የማይነግሩ ተማሪዎችን፣ እንደ ጾታ እና የወሲባዊነት መጎዳኘት (GSA) ክለቦች የሚገናኙ እና የሚደግፉ በተማሪዎች የሚመሩ ክበቦች አሏቸው። እነዚህ ክለቦች እንደማንኛውም ሌሎች ክለቦች ግልጽ በሆነ ዓላማ መመራት አለባቸው።
- በአከራካሪ እና ውስብስብ የህግ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረጋቸው ምክንያት ብቻ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ቡድን ከመፍጠር ሊያግዱ አይችሉም።

## ከክፍል ውጭ ትምህርት/ምሽቱን በሙሉ የሚቆይበት የመስክ ጉዞዎች

- ተማሪዎች ባረጋገጡት የፆታ መለያቸው ጋር በሚጣጣም ሁኔታ እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት።
- ስለመኝታ ቦታ/ሁኔታ ዝግጅት ከተማሪው/ዋ እና ከቤተሰብ (ቤተሰብ ተማሪውን/ተማሪዋን የሚደግፍ ከሆነ) ጋር መወያየት ያስፈልጋል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና ጥያቄ ከቀረበ፣ ሠላምና ደህንነት የተጠበቀና ማሸሚጠጥ የሌለበት አማራጭ የግል መኝታ አካባቢ የመሳሰለ መሰናዶ መሰጠት አለበት።
- ት/ቤቶች ማናቸውንም የግል ገበና ለመጠበቅ የሚፈልግ/የምትፈልግ ተማሪ ፣ በተቻለ መጠን ፣ ከሌሎች ተማሪዎች ባለማግለል ለማስተናገድ መሞከር አለባቸው።
- የተማሪ ጾታ የመቀየር አቋም ምስጢራዊ መረጃ እንደመሆኑ፣ ከመስክ ጉዞ ጋር በሚገናኝ ምክንያት፣ ከተማሪው(ዋ) እና/ወይም የተማሪው(ዋ) ወላጅ/ሞግዚት ይሁንታ ውጪ የትምህርት ቤት የሥራ ባልደረቦች ይፋ ማድረግ ወይም የተማሪ ጾታ መቀየርን አቋም ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለወላጆቻቸው/ለሞግዚቶቻቸው ይፋ ሊያደርጉ አይገባም።

## ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት እና የዛቻና ማስፈራራት ግምገማ

- LGBTQ ተማሪዎች ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራሪያ የሚገጥማቸው እድል ከፍተኛ ነው፣ እንዲሁም ራስን የማጥፋት አስተሳሰብ መጠናቸውም ከፍ ያለ ነው፣ እና LGBTQ ካልሆኑ ተማሪዎች ይልቅ ራሳቸውን ለማጥፋት የመሞከራቸው አድል ከአምስት እጥፍ በላይ ከፍ ያለ ነው።
- የቦርድ ፖሊሲ - "Board Policy JHF"፣ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ዛቻ - Bullying, harassment, or Intimidation ፣ ትምህርት ቤቶች ከማስፈራራት፣ ከማስጨነቅ፣ ከዛቻ ነፃ የሆኑ የትምህርት አካባቢዎች መሆናቸውን ስለማረጋገጥ የቦርዱን ቁርጠኝነት ከማሳየቱም በላይ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደምብ - "MCPS Regulation JHF-RA" ስለ ተማሪ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ዛቻ - Student Bullying, Harassment, or Intimidation፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ዛቻና ማስፈራራት የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል። እነዚህ በሚከተሉት የ MCPS ድረ-ገጾች ላይ ይገኛሉ https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jhf.pdf and https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jhfra.pdf።
- የቦርድ ፖሊሲ - "Board Policy COA" ስለ ተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም - Student Well-being and School Safety ስነምግባሮችን በመመርመር እና ተገቢውን የመከላከል ወይም የእርምት እርምጃዎችን በመውሰድ ሠላማዊ የትምህርት ቤት እና የሥራ አካባቢዎችን ስለመጠበቅ የባህርይና የስነምግባር ስጋቶችን የመከታተል-የመገምገም ሂደቶችን ዘርግቷል። ሁሉም ልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ ደህንነታቸውን የሚደግፍ

ሠላማዊና የሚያበለጽግ የትምህርት ቤት ድባብ እንዲኖራቸው ይገባል። ከቦርድ ፖሊሲ ACA አድሎአዊነት የሌለው፣ ፍትሃዊነት እና የባህል የብቃት ባህል ጋር የሚጣጣሙ የትምህርት ቤት ደህንነት እርምጃዎች በተማሪዎች እውነተኛ ወይም በይሆናል የግል ባህሪያቸው ተመስርቶ በአድሎ መተግበር የለበትም። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደምብ "MCPS Regulation COA-RA"፣ አስጊ ባህርይን መገምገም - Behavior Threat Assessment ፣ ላይ እንደተደነገገው በትምህርት ቤት ደረጃ የአስጊ ባህርይ መገምገምን ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት ያለባቸው ሠራተኞች ውስጣዊ መዛባትን ስለመረዳት እና የብዝሃነትን ግንዛቤ ስለማዳበር፣ እና ራስን ስለመጉዳት አስጊነት ወይም ራስን ስለመግደል ዝንባሌ እውቀት እንዲኖራቸው መሰልጠን እንዳለባቸው ተገልጿል። Board of Education Policy COA, Student Well-being and School Safety, and MCPS Regulation COA-RA, Behavior Threat Assessment, are available on the MCPS web at www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/coa.pdf and www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/coara.pdf

- ጉልበተኛነት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራት የሚያካትተው በተማሪው(ዋ) ላይ ያተኮረ ነባራዊ ወይም በግምታዊ አስተሳሰብ የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽን ነው፣ እናም ተማሪው(ዋ) በሚቀርበው/በምትቀርበው ጓደኛ ፣ የቤተሰብ አባል፣ ወይም ሌላ ሰው ወይም ቡድን ባህርይ ምክንያት በተማሪው(ዋ) ላይ ያነጣጠረ ድርጊትን ያካትታል።
- ቋንቋን እና/ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ ምስሎች እና ምልክቶችን ማሳየት፤ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው።
- በተማሪ ነባራዊ ሁኔታ ወይም በሚታሰበው የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ ምክንያት ተማሪ ላይ ያነጣጠረ ማግለል/አድሏዊነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራትን በሚመለከት የሚቀርብ ቅሬታ እንደሌሎቹ የአድሎአዊነት እና የትንኮሳ ቅሬታዎች ከሚስተናገዱበት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እርምጃ መወሰድ አለበት። ት/ቤቶች ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራትን በተመለከተ በንቃት መጠበቅ እና ወዲያውኑ መፍትሄ መስጠት አለባቸው።
- ጾታቸውን ስለቀየሩ ተማሪዎች እና ጾታ አስረግጠው ስለማይናገሩ ተማሪዎች በት/ቤታቸው ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ እና ተማሪዎች ጾታቸውን የመግለጽ ድፍረት እንዲያገኙ የት/ቤት ሠራተኞች ተገቢ/ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።
- ተማሪዎች ስለ እርግጠኛ የጾታ ማንነት ወይም ስለ ጾታ ዝንባሌ አገላለጻቸው ምክንያት የዲስፕሊን እርምጃ አይወሰድባቸውም።
- LGBTQ ተማሪዎች ላይ አፅንዖት በመስጠት ለሁሉም ተማሪዎች የጉልበተኝነት መከላከል ጉዳዮችን ለመፍታት ትምህርት ቤቶች ከእድሜ ጋር የተገናዘበ የተማሪ ድርጅቶች እንዲዘጋጁ እና እንዲመሩ ይበረታታሉ።

## ሰላማዊ ስፍራዎች

- መተላለፊያ/ኮሪዶር ወይም "ውልብ" ብሎ የሚታለፍበት አስፈላጊ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቶች ጾታ የቀየሩ ወይም ጾታቸውን ይፋ የማያደርጉ ተማሪዎች በማናቸውም ተማሪዎች ስጋት ሲኖርባቸው ወይም ምቾት በማይሰማቸው ጊዜ ሰላማዊ ወደ ሆነ ቦታ እንዲሄዱ (ለምሳሌ:- ዋና ቢሮ፣ የካውንስለር ቢሮ) ይፈቅዱላቸዋል።
- ሰላማዊ ክልሎች:- ትምህርት ቤቶች የአንዳንድ መምህራንን ማስተማሪያ ክፍሎች፣ የተለዩ ቢሮዎችን፣ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ማንኛውም ተማሪ በማንኛውም ምክንያት ከፍረጃ ነፃ እና ምቹና ከስጋት ነፃ የሚኮንበት ስፍራ/አካባቢ ይመድባሉ። በመዝጊያዎቻቸው ላይ "safe zone stickers" ያሏቸው የት/ቤት ሠራተኞች ሁሉን ያካተተ፣ የሚያረጋግጥ አካባቢ ስለማቅረብ አግባብነት ያለው ስልጠና ማግኘታቸውን ት/ቤቶች ማረጋገጥ አለባቸው።

## የሰራተኞች ድጋፍ

- የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Board of Education Policy ACA"፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትኃዊ፣ እና ባህላዊ ብቃት - Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency የ MCPS ሠራተኞችን በጠቅላላ ከማናቸውም አይነት አድሎ፣ ግለሰቦችን በትክክለኛ ወይም በሚገመት-ነው ተብሎ በሚታሰብ ባህርያቸው ምክንያት እና በጥላቻ ድርጊት፣ ጠብ፣ ጭቅጭቅና ረብሻ፣ ይልኙታቢስነት፣ ክብር መንሣት፣ ወይም የቃል ስድብ፣ ዛቻና ማስፈራራት፣ አካላዊ ድብድብና ግጭት፣ ዝርፊያ፣ ወይም ንብረት ማበላሸት ከመሣሰሉት ብቀላዎች፣ — ትምህርትን ወይም የሥራ አካባቢን የሚያደናቅፍ፣ እና ዘረኝነትን፣ ወንድና ሴትን እኩል አለማየትን፣ እና ጾታን የሚመለከቱ ጉዳዮችን፣ እና ሌሎች ተቋማዊ አገላለጽ ያላቸውን ፍትኃዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን በሙሉ ይከለክላል። የሥርዓተ-ፆታ ማንነት ጉዳዮችን ያካተተ መመሪያ እና ድጋፍ የሚሹ ሠራተኞች በ 240-740-2888 ደውለው "Office of Human Resources and Development, Department of Compliance and Investigations" አስተባባሪውን እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ህትመት፡- Department of Materials Management for the
Office of Districtwide Services and Supports

0860.22ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 9/22 • NP